| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "አኃዛውያን ፡ ልቅሞች ። " |
| ርእስ ፤ | "የነዋሪዎች ፡ አሰፋፈር ፡ ችምችማት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ክፍላተ ፡ ሀገር ፤ (የነዋሪ ፡ ብዛት ፡ በኪሎሜትር ፡ ማእዘን ፥ ለ 2013 ፡ ዓ.ም. ። )" |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ታኅሣሥ ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቀ.2013-002 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | (ስሕተቶች ፡ በተገኙ ፡ ወይ ፡ በተጠቈሙ ፡ ቍጥር ፡ ታርመው ፥ ዝርዝራቸው ፡ ዳግመኛ ፡ ይወጣል ። ) |


# የነዋሪዎች ፡ አሰፋፈር ፡ ችምችማት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ክፍላተ ፡ ሀገር ፤

(የነዋሪ ፡ ብዛት ፡ በኪሎሜትር ፡ ማእዘን ፥ ለ 2013 ፡ ዓ.ም. ። )




**መናገሻ ፡ አውራጃ** ፤ 941 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
(ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ) ፤ (2 737 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$)
**ሸዋ** ፤ 206 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
(መናገሻ ፡ አውራጃን ፡ ጨምሮ ፥ 280 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$)
**ወሎ** ፤ 153 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ስሜን ፡ እና ፡ በጌምድር** ፤ 146 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ጐዣም** ፤ 206 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ትግራይ** ፤ 112 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ሲዳሞ** ፤ 67 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ሐረርጌ** ፤ 26 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ጋሞ ፡ ጎፋ** ፤ 160 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ከፋ** ፤ 116 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ዐሩሲ ፡** (ኀሩሲ) ፤ 224 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ወለጋ** ፤ 59 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ኤርትራ ፡** (ባሕር ፡ ምድር ፡ እና ፡ ደንከል) ፤ 18 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ኢሉባቦር** ፤ 78 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ባሌ** ፤ 30 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$
**ኢትዮጵያ** ፤ 87.7 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$

—

[ ] ፡ ከ 1-25 ፡ ነዋሪ ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 1-50 ፡ ነዋሪ ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 50-100 ፡ ነዋሪ ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 100-150 ፡ ነዋሪ ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 150-200 ፡ ነዋሪ ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 200-250 ፡ ነዋሪ ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 250-300 ፡ ነዋሪ ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 300-1000 ፡ ነዋሪ ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤
[ ] ፡ ከ 1000+ ፡ ነዋሪ ፡ በ ፡ ኪ.ሜ $^2$ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።

የኢትዮጵያ ፡ ክፍላተ ፡ ሀገር ፡ ነዋሪዎች ፡ አሰፋፈር ፡ ችምችማት ፡ (density) ፡ በተወሰነ ፡ ደረጃ ፡ ምኅዳርንና ፡ የማእከላዊ ፡ መንግሥትን ፡ ታሪካዊ ፡ ኑባሬ ፡ ይከተላል ። እላይ ፡ የተዘረዘረው ፡ ያሰፋፈር ፡ ችምችማት ፡ አኃዝ ፡ ለእየክፍላተ ፡ ሀገሩ ፡ አማካይ ፡ አኃዝ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ ባውራጃ ፡ እና ፡ በወረዳ ፡ ደረጃ ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ አያመለክትም ።

**1. ፲ ምኅዳራዊ ፡ ተጽዕኖ ።**

በጠቅላላው ፥ ከቈላ ፡ (ከ 1500 ፡ ሜትር ፡ ከፍታ ፡ በታች ፡ የሚገኝ ፡ አካባቢ) ፡ ይልቅ ፡ ወይና ፡ ደጋን ፡ (ከ 1500 ፡ ሜትር ፡ እስከ ፡ 2500 ፡ ሜትር ፡ ከፍታ ፡ የሚገኝ ፡ አካባቢን) ፡ እና ፡ ደጋን ፡ (ከ 2500 ፡ ሜትር ፡ ከፍታ ፡ በላይ ፡ የሚገኝ ፡ አካባቢን) ፡ በውሃ ፡ በልምላሜ ፥ እንዲሁም ፡ በአየር ፡ ጠባይ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ባለው ፡ ተስማሚነት ፡ ምክንያት ፥ አብዛኛው ፡ ነዋሪ ፡ ለኑሮው ፡ ይመርጠዋል ። በዚህም ፡ ምክንያት ፥ የነዋሪው ፡ አሰፋፈር ፡ ችምችማት ፡ ለረዥም ፡ ዘመን ፡ ከፍ ፡ ያለባቸው ፡ አካባቢዎች ፥ የደንና ፡ የተፈጥሮ ፡ ሽፋናቸው ፡ እየተመናመነ ፥ ለዐፈር ፡ መሸርሸርና ፡ ለድርቅ ፡ እየተዳረጉም ፥ ወደ ፡ በረሓነት ፡ ተለውጠዋል ። በተለይ ፡ በሰሜናዊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍሎች ፥ በትግራይ ፣ በባሕር ፡ ምድር ፣ እንዲሁም ፡ በወሎ ፡ እና ፡ በሰሜን ፡ ሸዋ ፡ አካባቢዎች ፡ ይህ ፡ ጉዳት ፡ ደርሷል ።

**2. ፲ የማእከላዊ ፡ መንግሥት ፡ ኑባሬ ፡ ተጽዕኖ ።**

የማእከላዊ ፡ መንግሥት ፡ ምኅዳራዊ ፡ ተጽዕኖ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የቀድሞ ፡ እና ፡ ያኹን ፡ መዲናዎች ፡ የነዋሪዎች ፡ ችምችማት ፡ ይታያል ። ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከመመሥረቷ ፡ ካ 1879 ፡ ዓ.ም. ፡ በፊት ፥ አካባቢው ፡ በኪሎሜትር ፡ ማእዘን ፡ ከ 2 ና ፡ ከ 3 ፡ ነዋሪዎች ፡ በላይ ፡ እንዳልነበረው ፡ ይታመናል ። ዛሬ ፥ ካንድ ፡ ሺሕ ፡ ነዋሪዎች ፡ በኪሎሜትር ፡ ማእዘን ፡ የሚበልጥ ፡ ችምችማት ፡ አለው ። እንዲሁም ፡ አንኮበር ፣ ጐንደር ፣ መቀሌ ፣ ላሊበላ ፣ አኵስም ፣ ወዘተርፈ ።

**3. ፲ የክፍለ ፡ ሀገር ፡ አማካይ ፡ ችምችማት ።**

የክፍለ ፡ ሀገር ፡ አማካይ ፡ ችምችማት ፡ ያውራጃ ፡ እና ፡ የወረዳ ፡ ልዩነቶችን ፡ አይገልጽም ። ለምሳሌ ፥ ለሲዳሞ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ የተገኘው ፡ አማካይ ፡ ችምችማት ፡ 67 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$ ፡ ሲኾን ፥ በክፍለ ፡ ሀገሩ ፡ ውስጥ ፥ ካውራጃ ፡ አውራጃ ፣ ከወረዳ ፡ ወረዳ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ልዩነት ፡ አለ ። በሲዳማ ፡ አውራጃ ፡ እስከ ፡ 250 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$ ፡ ችምችማት ፡ የሚታየውን ፡ ያኽል ፥ በሰፊው ፡ የበቦረና ፡ (ነጌሌ) ፡ አውራጃ ፡ ደግሞ ፡ ያሰፋፈር ፡ ችምችማቱ ፡ ከ 3 ፡ ነ/ኪ.ሜ $^2$ ፡ አይበልጥም ።

በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባውራጃ ፡ እና ፡ በወረዳ ፡ ደረጃ ፡ ያለውን ፡ ያሰፋፈር ፡ ችምችማት ፡ የሚያመለክት ፡ አኃዛዊ ፡ መረጃ ፡ በቅርቡ ፡ ይቀርባል ❖


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።